የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FFDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፭
አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 65
ADDIS ABABA 9th November 2009

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፷፯/፪ሺ፩

የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ገጽ ፭ሺ፵፭

CONTENTS

Regulation No. 167/2009

Federal Hospitals Administration Council of Ministers Regulation ...... ...................................... Page 5045
Corridgendum No. 8/2009..........................................page 5050

### ደንብ ቁጥር ፩፻፷፯/፪ሺ፩

### ስለፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ (በአዋጅ ቁጥር ፮፻፫/፪ሺ፩ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርእስ

ይህ ደንብ "የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፯/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "የፌዴራል ሆስፒታል" ማለት ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሆነ ሆስፒታል ወይም በዩኒቨርሲቲ ስር የሚተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫና የጤና ሙያ ማስተማሪያ ሆስፒታል ነው፤

፪/ "የግል ሕክምና መስጫ ክፍል" ማለት በፌዴራል ሆስፒታል ውስጥ የጤና ባለሙያዎች የህክምናና የምርመራ አገልግሎት በመስጠት ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ነው ፤

፫/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

### *Regulation No. 167/2009*
### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF FEDERAL HOSPITALS*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 (as amended by Proclamation No. 603/2008).

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Federal Hospitals Administration Council of Ministers Regulation No. 167/2009".

2. *Definitions*

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ "Federal Hospital" means a hospital accountable to the Ministry of Health or a health service delivery and teaching hospital under a university;

2/ "Private Wing" means a system established within a federal hospital whereby health professionals provide medical and diagnostic services and obtain benefits from fees collected;

3/ "Ministry" and "Minister" means the Ministry and Minster of Health, respectively;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.10

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፬/ "ዩኒቨርስቲ" ማለት የጤና ሙያ ማስተማሪያና የጤና አገልግሎት መስጫ ሆስፒታልን የሚያስተዳድር የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው፡፡

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በማንኛውም የፌዴራል ሆስፒታል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬. የፌዴራል ሆስፒታል ሥልጣንና ተግባር

የፌዴራል ሆስፒታል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል:-

፩/ የመደበኛና ድንገተኛ ምርመራና ህክምና አገልግሎት ይሰጣል፤

፪/ የሪፈራል አገልግሎት ይሰጣል፤

፫/ የህክምናና የምርመራ አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የምርምር ተግባራትን ያከናውናል ፤

፬/ የማስተማሪያ ሆስፒታል ሲሆን፣ በሆስፒታሉ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ወይም ስልጠና የጤና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዳ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፭/ የማህበራዊና የማገገሚያ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፮/ ለተመላላሽና ተኝተው ለሚታከሙ ተገልጋዮች የበሽታን መከላከልና የጤና ማጎልበት ተግባር ያከናውናል፤

፯/ የህብረተሰቡን ጤና እና ጤና-ነክ ችግሮችን በመፈተሽና በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይጠቁማል፤

፰/ ለሌሎች የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የአቅም ግንባታና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

፱/ የሚያከናውናቸውን የጤና አገልግሎቶች በተመለከተ መረጃ ይሰበስባል፣ አግባብ ላለው አካልም ያስተላልፋል፤

፲/ ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፲፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሠሳል፡፡

፭. የፌዴራል ሆስፒታል አቋም

፩/ የአመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) ፣

፪/ በቦርዱ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሚሾም ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

4/ "University" means a government higher education institution that runs a teaching and health service delivery hospital.

3. *Scope of Application*

This Regulation shall be applicable in all Federal Hospitals.

4. *Powers and Duties of Federal Hospitals*

Any federal hospital shall have the powers and duties to:

1/ provide regular and emergency medical and diagnostic services;

2/ provide referral services;

3/ undertake applied research activities to improve the quality of health services;

4/ in case of a teaching hospital, ensure that health services provided in the hospital are not compromised for training or educational purposes;

5/ provide social and rehabilitative services;

6/ ensure provision of the relevant preventive and promotive health care for outpatients and inpatients;

7/ assess and identify the health and health related problems of the community and forward feasible recommendations;

8/ provide technical assistance and capacity building to other health facilities;

9/ collect health information data regarding services provided and report the same to the appropriate body;

10/ collect service fees;

11/ own property, enter into contract, sue and be sued in its own name.

5. *Organization of Federal Hospitals*

A federal hospital shall have:

1/ A Governing Board (hereinafter the "Board");

2/ Chief Executive Officer to be nominated by the Board and appointed by the Minister or the concerned University President; and

3/ the necessary staff.

፮. <u>ስለቦርድ አባላት</u>

፩/ ቦርዱ በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሚሰየሙ ከአካባቢው መስተዳደር፣ ከሚመለከታቸው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ ከትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ከሲቪክ ማህበራትና ከታዋቂ ሰዎች የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል፡፡

፪/ የቦርዱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ይወሰናል ፡፡

፫/ ለቦርድ አባላት የሚከፈለው አበል አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በሚኒስትሩ ይወሰናል፡፡

፯. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የፌዴራል ሆስፒታል ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ ሆስፒታሉን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪/ የሆስፒታሉን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት መርምሮ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፫/ ሆስፒታሉ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን የክፍያ ተመን አስመልክቶ የሚያቀርበውን የማሻሻያ ሀሳብ በመመርመር አስተያየቱን ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤

፬/ የሆስፒታሉን የውስጥ አሰራር መመሪያዎች ያፀድቃል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

፭/ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲያስችለው ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥራቸውንም ይመራል፤

፮/ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ከሆስፒታሉ ተጠንቶ የቀረበለትን ጥናት በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤

፯/ በሆስፒታሉ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ተገቢውንም ውሳኔ ይሰጣል፤

፰/ የሆስፒታሉ የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ከመቅረቡ በፊት መርምሮ ያጸድቃል፡፡

6. *Members of the Board*

1/ Members the Board shall be designated by the Minister or the concerned University President from the local administration, the relevant sectoral offices, teaching and academic institutions, civic societies and influential persons.

2/ The number of members of the Board shall be determined by the Minister or the concerned University President.

3/ Allowance to be paid to Board members shall be fixed by the Minister in accordance with the relevant law.

7. *Powers and Duties of the Board*

The Board of a federal hospital shall have the powers and duties to:

1/ oversee and supervise the administration of the hospital;

2/ examine and submit to the Ministry or the concerned University President the annual work plan and budget of the hospital, and follow up the implementation of the same upon approval;

3/ examine and forward recommendation to the Ministry or the concerned University President service fees rate revision proposed by the hospital;

4/ approve the internal rules of procedures of the hospital and follow-up the implementation of the same;

5/ establish and direct committees to effectively perform its duties;

6/ decide on studies and proposals of the hospital regarding the establishment of private wing health services;

7/ investigate and decide on complaints lodged against the hospital;

8/ examine and approve performance and financial reports of the hospital prior to their submission to the Ministry or the concerned University President.

## ፰. የቦርዱ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከአባላቱ አንድ ሦስተኛው ስብሰባ እንዲካሄድ ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፪/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል ፡፡

## ፱. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን

፩/ የአንድ የቦርድ አባል የሥራ ዘመን ለሦስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ እንደገና እንዲያገለግል ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ባላቸው የሥራ ኃላፊነት ምክንያት የቦርድ አባል የሆኑትን ሰዎች የአገልግሎት የሥራ ዘመን አይመለከታቸውም ፡፡

፫/ ማንኛውም የቦርድ አባል የአገልግሎት ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ከአባልነት መሰናበት ቢፈልግ ይህንኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሲጠናቀቅ የነባሩ ቦርድ ሰብሳቢ ከስድስት ወራት ለማይበልጥ ጊዜ በቀጣዩ ቦርድ ውስጥ በአባልነት እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## ፲. ከቦርድ አባልነት ስለመነሳትና የጎደሉትን ስለመተካት

፩/ አንድ የቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊነሳ ይችላል፡-

ሀ) በቦርድ አባሉና በሆስፒታሉ መካከል የጥቅም ግጭት ሲያጋጥም፤

ለ) የጤና እክል ወይም የስነ-ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም፤

ሐ) በወንጀል ተከሶ ከተፈረደበት፤

መ) ያለምንም ፈቃድ ወይም አስቀድሞ ባለ ማሳወቅ ለሦስት ተከታታይ ጊዜ የቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ ቀሪ ሲሆንና በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሳያሻሽል ሲቀር፡፡

፪/ አንድ የቦርድ አባል ከአባልነት ሲነሳ ሚኒስትሩ ወይም ፕሬዝዳንቱ አዲስ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡

## 8. *Meetings of the Board*

1/ The Board shall meet once in a month; provided however, that it may meet at any time at the call of the chairperson or the request of one-third of its members.

2/ There shall be a quorum when the majority of the members of the Board are present at a meeting.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority vote; and in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may issue its own rules of procedures.

## 9. *Terms of Board Membership*

1/ The term of board membership shall be for three years; provided however, that membership may be extended for only one additional term.

2/ Not withstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the duration of membership shall not be applicable for those members holding membership due to their responsibility in the office.

3. Any Board member wishing to end his membership of the Board prior to the expiry of his term of service shall notify the Board.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, when the term of office of Board members expires, the chairperson of the existing Board shall serve as a member in the incoming board for a period not exceeding six months.

## 10. *Removal and Substitution of Board Members*

1/ A member may be removed from Board membership for the following reasons:

(a) when a conflict of interest arises between him and the hospital;

(b) due to health or ethical problems;

(c) when sentenced by a court of law;

(d) for failure to be present at three consecutive meetings of the Board without any permission or prior notification and failure to improve such conduct following a written warning.

2. When a Board member is removed from membership, the Minister or President shall approve a replacement Board member.

## ፲፩. የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር

፩/ የፌዴራል ሆስፒታል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የሆስፒታሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈፃሚው:-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተመለከቱትን የሆስፒታሉን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የሆስፒታሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ለቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፤

ሐ) የሆስፒታሉን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግ ራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለሆስፒታሉ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ሆስፒታሉ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው ተገቢውን የሰው ሀይልና ሌሎች ግብዓቶችን ያሟላል፤

ረ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴዎችን ያቋቁ ማል፣ ሥራቸውን ይመራል፣ ያስተባ ብራል፤

ሰ) የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል እንዲረዳ ህክምናና ህክምና ነክ ያልሆኑ ሥራዎች በሦስተኛ ወገኖች ስለሚሰጡ በት ሁኔታ በማጥናት ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሸ) በሆስፒታሉ ውስጥ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ስለሚቋ ቋሙበት ሁኔታ እያጠና ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ቀ) ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤

በ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙ ነቶች ሆስፒታሉን ይወክላል፤

ተ) የሆስፒታሉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ቸ) ከቦርዱ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፫/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ለሆስፒታሉ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሆስፒታሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 11. *Power and Duties of the Chief Executive Officer*

1/ The Chief Executive Officer of a federal hospital shall, subject to the general directives of the Board, direct and administer the activities of the hospital.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Chief Executive Officer shall:

(a) exercise the powers and duties of the hospital specified under Article 4 of this Regulation;

(b) employ and administer the employees of the hospital in accordance with directives to be approved by the Government following the basic principles of the civil service laws; submit to the Board for approval the selection, placement and dismissal of officials accountable to him;

(c) prepare and submit to the Board the annual work program and budget of the hospital and implement the same upon approval;

(d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the hospital;

(e) ensure the adequate availability of human and other resources to enable the hospital to discharge its activities;

(f) establish committees when necessary and direct and coordinate their activities;

(g) undertake studies, and submit to the Board, on outsourcing clinical and non-clinical services to improve overall quality of health care, and implement the same upon approval;

(h) undertake studies, and submit to the Board, on the establishment and operation of private wings, and implement the same upon approval;

(i) serve as non-voting member and secretary of the Board;

(j) represent the hospital in its dealings with third parties;

(k) submit to the Board the performance and financial reports of the hospital;

(l) perform other duties assigned to him by the Board.

3/ The Chief Executive Officer may delegate part of his powers and duties to the officials and employees of the hospital to the extent necessary for the efficient performance of its activities.

**፲፪. ስለግል ህክምና መስጫ ክፍሎች**

፩/ እያንዳንዱ የፌዴራል ሆስፒታል በውስጡ የግል የህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ያቋቁማል፡፡

፪/ በግል የሕክምና መስጫ ክፍል የሚሰጠው አገልግሎት ሆስፒታሉ በመደበኛ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል የሚሰጠውን አገልግሎት የማያስተጓጉል መሆን አለበት ፡፡

፫/ በመደበኛውና በግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጠው ባለሙያ በሚሰጠው የሕክምናና የምርመራ አገልግሎት በተጠቃሚዎች መካከል ልዩነት መፍጠር የለበትም፡፡

፬/ ለግል የህክምና መስጫ አገልግሎት የሚያስ ፈልገው የሥራ ክፍል ብዛት እንደሁኔታው እየታየ በቦርዱ ይወሰናል፡፡

**፲፫. በጀት**

የፌዴራል ሆስፒታል በጀት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲፬. ስለሂሳብ መዛግብት**

፩/ ማንኛውም የፌዴራል ሆስፒታል የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የፌዴራል ሆስፒታል የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይመረመራል ፡፡

**፲፭. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

**፲፮. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ፡፡

**፲፯. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

12. *Private Wing Health Service Units*

1) Each federal hospital shall establish a private wing health service unit.
2) A private wing health service provision shall be practiced provided that its operation does not negatively affect the regular operations of the hospital services.
3) There shall not be discrimination against patients by medical staff providing services in the regular and the private wing of the hospital.
4) The Board shall decide the number of service rooms for the private wing.

13. *Budget*

The budget of a federal hospital shall be allocated by the Government in accordance with the relevant laws.

14. *Books of Accounts*

1) Any federal hospital shall keep complete and accurate books of accounts.
2) The books of accounts and financial documents of a federal hospital shall be audited annually by the Auditor General.

15. *Power to Issue Directives*

The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

16. *Inapplicable Laws*

No regulations, directives or practices shall, in so far as they are inconsistent with the provisions of this Regulation, have effect with respect to matters provided herein.

17. Effective Date

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 9th day of November, 2009.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

Corridgendum No. 8/2009

The Amharic version of Article -3 of the Ethiopian Postal Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No 165/2009 has no equivalent English version thus it is helely corrected by the following English version of Article -3 and for the succeeding Article of the English version which reads as "3" is also hereby corrected as "4"

" 3. Supervising Authority

The Ministry of Transport and Communication shall be the supervising authority of the Enterprise."